# Geberekidan Desta and his unrestrained hate against Emperor Menlik. By Getachew Reda (Editor Ethiopian Semay)

ጐጠኛው ገብረኪዳን ደስታና ታሪክ አላዋቂነቱ ዛሬም እየደገመው ነው! ቃለ መጠይቁን በሚከተለው አድራሻ ያድምጡ http://aigaforum.com/audiovideo/Interview_with_the_Author_of_Embita__Antsar_Wereretі__3.mp3 (የትግርኛው ትርጉም እዚህ አቅርቤዋለሁ)

ገብረኪዳን ደስታ ማነው? ገብረኪዳን ደስታ ማለት በአፄ ሃይለስላሴ ጊዜ መምህር የነበረ፤ በደርግ ወቅትም ወደ ጫካ በመሄድ ወያኔን ተቀላቅሎ የወያኔ ታጋይ የነበረ፤ከዚያም ወደ ደርግ በመቀላቀል ወያኔን ከድቶ ለደርግ እጁን በመስጠት፤ (ወይንም ዛሬ አሜሪካ ውስጥ በጥገኝነት እየኖረች "በገዛ ተጋሩ ፓልቶክ ውስጥ "ተቃዋሚውን በመዝለፍና በማዋረድ" ያለ ዕውቀቷ ስትዘባርቅ የምታመሽው አንደ እነ አልማዝ በቀለ (ድሮ የአክሱም አብርሃ ወአጽብሃ ት/ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ የነበሩት የመምህር በቀለ ታደሰ ልጅ የሆነች) ጫካ ውስጥ በትግሉ ወቅት በደረግ ጊዜ በወያኔ ከፍተኛ አመራሮች ውሳኔ ያለ ፍላጐቷ ወንድ ምረጪ ተብላ (ብታንገራግርም፤ የድርጅት ተልዕኮ ስለሆነ) በትእዛዙ መሰረት የታዘዘቺው በመፈጸም ከመረጠቺው ታጋይ ጋር ግብረ ስጋ በመፈጸም ለሽፋን አንዲያመች እርግዝና እንድትይዝ ተደርጐ እርጉዝናዋን ይዛ ወደ ከተማ ገብታ ወያኔን ከድታ አንደገባች በማስመሰል ለስለላ አንደተላከቺው ዓይነት- ገብረኪዳንም ወደ ደርግ ገብቶ የደረግ ፕሮፓጋንዳ እያናፈሰ ወያኔን ኩፉኛ በማውገዝ ወደ ደርግ እጁ የሰጠበት ምክንያት ለስለላ በሽፋን ተልኮ የነበረ ሊሆን ይችላል እያሉ አንዳንዶቹ ጥርጣሬያቸውን ያስቀምጣሉ። አንዳንዶቹም ፤ የምሩ ከድቶ ነበር ይላሉ።)

ከዚያም በመምህርነት ሙያው በመቀጠል ሲሰራ ቆይቶ አንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ወያኔ በመቀላቀል በውዝፍ አንጠልጥሎት የነበረውን የትግራይ ቄሶችን በሌኒንስት ማርክሲስትና ማኦይስት ትግራይ ርዕዮተ ዓለም በማጥመቅ በየገዳማቱ የቤተ ክህነት ትምህርት የቀሰሙ የወያኔ ካድሬዎችን የክህነት ልብስ በማልበስና ጥምጣም በማስጠምጠም እስከ ዋልድባ ድረስ ሰርገው በመግባት በየገዳማቱ የሚገኙ የአብያተ ክርስትያናት ንብረትም ሆነ አባሎች በወያኔ ስር እንዲተዳደሩና በመንገዱ አንዲጓዙ ያደረገ ነው። ግለሰቡ ጸረ- ኦርቶዶክሳዊ እርምጃዎችን እንዲከናወን የመራና ከሃይማኖት-ቢሶቹ ከወያኔ መሪዎች ጋር በዚህ ተግባር የተባበረ፤ የሰማይ ቤት ኩነኔ የማይፈራ፤ "ቄሶች ክላሺን ኮቭ" ጠመንጃ ታጥቀው በማርካሰዊ ርዕዮት ተጠምቀው ለትግራይ ብሔረተኛነት በመቆም ጦርነት ውስጥ በመቀላቀል አንዲዋጉ እና የአምላክ ፍጡር የሆነውን

ወደ ሰው ልጅ ጥይት በመተኰስ ሰው እንዲገድሉ ካስተማሩዋቸው የወያኔው ቤተክህነት-ክንፍ አደራጆች መካከል አንደኛው እና ትልቁ ካድሬአቸው የነበረ ነው።

መምህር ገብረኪዳን ደስታ "የትግራይ ሕዝብና የትምክሕተኞች ሴራ" የሚል እጅግ አሳፋሪ ጠባብ የብሔረተኛ መጽሐፍ የጻፈ፡ የሸዋ አማራ እና በጠቅላላ አማራው ሕበረተሰብን የዘለፈ፤ የናቀ፤ ያዋረደ፤ የአማራ ሕዝብ ጉብዝናውን ለመግፈፍ የተቻለውን ያህል ውሸት በመፍጠር ብዙ የአማራ ተወላጆች እና ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ያስቀየመ፤ ነው።

የእንደርታ እና የራያዎቹ የትግርኛ ልሳን ወደ "አ. ሽ .ዓ." (አክሱም ሽሬ ዓድዋ) ዎቹ ልሳን ለመለወጥ እንዲያመቸው ዛሬ ትግራይ ውስጥ መቀሌ ከተማ መኖርያው ካደረጉት መካካል፤በዕድሜ 'አዛውንት' በሕሊና አስተሳሰቡ ግን ከመንደርተኝነት ባሻገር ያላደገ፤እጅግ ጠባብ እና ትምክሕተኛ ከሆኑት የወያኔ መሰሪዎች እና ትምክሕተኞች መካከል አንዱ ነው።ለዛው ከላይ ለተጠቀሰው ጐጠኛና ከፋፋይ መጽሐፉ "ይድረስ ለጎጠኛው መምህር" የተባለው መጽሐፌ የጻፍኩትም፤ለዚህ ግለሰብ መጽሐፍ ምላሽ ነበር።

ወደ ቃለ መጠይቁ ትርጉም ከመግባቴ በፊት ከላይ የጠቀስኩት የትግርኛ አጠቃቀም ዘመቻቸው በሚመለከት ጥቂት ልበልና ወደ እዚያው እናመራለን።

የዛና ተወላጅ (ሽሬ አውራጃ ውስጥ የምትገኝ ትንሽ ገጠር ) የሆነው ገብረ ኪዳን ዛሬ እንደርታ አውራጃ መቀሌ ከተማ ውስጥ እየኖረ፤ የአማርኛ ቃላቶች ከትግርኛ ቋንቋ ለማጥራት ስለ ትግርኛ "ጥራት" ከሚንገበገብና በጠባብነት ስሜት ከሰከሩት ከነ ሰለሞን ዕንቋይ፤ እና በመሳሰሉት የወያኔ "ኤጥኒቆሶች" ጸረ አማርኛ ቋንቋ ከሚዘምቱት  መካከል አንዱ ነው። ወያኔ ጫካ ሲገባ ሕዝባችን ትግርኛው በአማርኛ ተመርዞ "በትግርኛ ቋንቋ" እንዳይናገር በመደረጉ "ቋንቋው" እንዲያውቅ እንታገላለን ብለው ሲሸፍቱ፤ ከጫካ ይዘውለት የመጡት አማርኛን የሚተኩ ቃላቶች  ግን "እንግሊዝኛ፤ዓረብኛ እና ኤርትርኛ" ቃላት እና ልሳን ነበር።

ገብረኪዳን ይህንን ሴራ ያውቃል። አጅግ የሚገርመው ደግሞ "ወያኔ ወደ መንግሥትነት የተሸጋገረበት፤ "ሽግግር" ብሎ፡ የጠራው እርሱ እራሱ (ገብረኪዳን) የፓርላማ አባል በነበረበት ጊዜ "ዞን፤ሊስ፤...ወዘተ...ወዘተ..." የሚባሉ የእንግሊዝኛ እና የመሳሰሉ የባዕድ ቃላቶች በሕገ መንግሥታቸው ሲጸድቅ በደስታ ተቀብሎ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን የማናውቅ መስሎት "ከ አ.ሽ.ዓ. (ከአክሱም፤ከሽሬና ከዓድዋ) የተለየ የትግርኛ ልሳን እና የአማርኛ፤ ኦሮምኛ፤ አገው፤ዓፋርኛ ቃላቶችን እየቀላቀሉ ለብዙ ሺሕ አመት የሚናገሩ (የእንደርታ ራያ፤ተምቤን ....ለምሳሌ ይጠቀሳሉ፡) ከ አ.ሽ.ዓ. ትግርኛ አካባቢ ሕብረተሰብ

ለየት ባለ መልኩ የሚነገር የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማሕበረሰብ ልዩነት አንጻለ እያወቁ፡ በላያቸው ላይ የቋንቋ ለውጥ ዘመቻ ለማከናወን በመጣር ላይ ይገኛሉ።

በእነኚህ ሰፋፊ የትግራይ አውራጃዎች የራሳቸው ዘይቤ እና የቃላት አሰካክ ተቀባይ ሆኖ አለ ምንም የመረዳጃ ችግር ሳይፈጠር እየተነገረበት መቆየቱና ተቀባይነት አግኝቶ ለሺዎቹ ዘመናት ሲነገርበት መቆየቱ እየታወቀ፤ ዛሬ እነ ገብረኪዳን ደስታ በስታሊኒዝም እና ማኦይዝም የሰከረ የደደቢት ሕሊና ተጠምቀው፤ ለዘመናት የኖረ ባሕላዊ እና ቋንቋዊ የአጠቃቀም ዘይቤ በመጻረር ፡ "መንግሥታዊ የቋንቋ አጥር እና ህግ በመቀየስ ፤ቅጣት በመፈጸም" አማርኛ የሚባል ቃላት ብቻ ***(እንግሊዘኛ እና ዓረብኛን አይነኩም። ሊዝ፤ ዞን የሚለውን የእንግሊዞች ባዕዳኖቹ ቃላት በሕግ አጽድቀው የሚጠቀሙባቸውን ማስተዋል ያስፈልጋልለ።)*** ከትግርኛ እየተለቀመ ካልወጣ ትግርኛችን "ትግርኛ" ሊባል አይችልም! በማለት አንድ "ወጥ የሆነ" የጥቂት አውራጃዎች የትግርኛ የልሳን እና የቃላት አጠቃቀም ወደ በሌሎቹ አውራጃዎች ላይ በመጫን፤ በዜና ማሰራጪያዎቻቸው በኩል እያስሰረጹ እና እያስተማሩ (ትምህርት ተቋማት ሁሉ ሳይቀሩ) የሌሎችን ሕጋዊና ባሕላዊ የልሳንና የቋንቋ "አጠቃቀም" መብት እየተጋፉ፤ "ንብ ከአበባ" "ሰው፤ከቋንቋ ገበያ" ለመለያየት የሚያደርጉት እጅግ አስነዋሪ የቋንቋ ጽዳት (አማሃሪክ ላንጌች- ክሊንሲንግ) እንዲካሄድ ግምባር ቀደም ሚና እየተንቀሳቀሱ ይገኛል።

በነገራችን ላይ የወያኔ ቴ/ቪዥን እና የራዲዮን አዘጋጆቻው እና ዜና አቅራቢዎቻቸው ላዳመጠ ሰው የሚጠቀሙበት የትግርኛ ዘይቤ እና የቃላቶች (የኪነት ዘፋኞች፤ገጣሚዎችና ተዋናያኖች፤ ሳይቀሩ) አጠቃቀም ፈሊጥ በጣም በሚገርምና አሳሳቢ ሁኔታ የደረሰ መሆኑን ልብ ላለ ሰው መገንዘብ አያዳግተውም። የዜና አንባቢዎቻቸውና ከላይ የጠቀስኢኳቸው የኪነት ባለ ሙያዎች የኤርትራዊያኖችን ልሳን ለመጥለፍ ይቃጣቸዋል፤ አንዳንዶቹም ጭራሽኑ የ አ .ሸ .ዓ ልሳን እና ቃላት በመጠቀም በጽሑፍ እና በደምፅ የሚዉሉ ጥሬ ቃላቶች፤ ላይ የሚተላለፈው የዜና ስርዓተ ቋንቋ አቀራረባቸው ስንታዘብ ጭራሽኑ ለትዝብት በሚጥል ሁኔታ ተሸጋግሮ እናያለን። ይህ ደግሞ በሕብረተሰባዊ የተፈጥሮ የቋንቋ ግብይት የመጣ ሳይሆን ሆን ተብሎ በወያኔ ሚዲያ እና ሴራ ተልዕኮው እንዲስፋፋ እየተደረገ ነው ።

የራያና አዘቦ ወይንም አንደርታ **ገበሬ/አራሹ ክፍል** ለምሳሌ "ሳሪሃ መሪሃ" "እሽ ኢሉ" "ሃምዚ ኸዚ" "ዳአም" "ናጋ" "ሃሳስ" "ከንዲ ግዛዕ"፤ "ጭልቓ" "ጨለ" "ባዓል ስልጣን" የሚሉ ቃላቶችን፤

"ገለመለ" "ስቕ ኢሉ" "ከመዚ ሕጂ" "ይኹን እምበር" ፤እንተኾነውን" "ጽባሕ" "ገልጣም" "ከንዲ ገለ" "ጠዓሞት" "ሕራይ" "መዚ"...በሚሉ የ "አሸዓ'/ ኤርትራኛ ቃላቶች በመለወጥ አንድ አውራጃ ባንድ አውራጃ የቋንቋ ብልጠትና ትምክሕት

ወረርሺኝ “የ ዞር ጫና /ንዮ ኮሎኒያል ኮንስፒራሲ/ ሴራው ያለ ተቃውሞ ሲካሄድ ስታዘብ በጣም ይገርመኛል።

አብዛኛዎቹ ከእንደርታ እና ራያ ተምቤን... ወያኔን ተቀላቅለው ከጫካ ከተመለሱ በኋላ የሚጠቀሙበት የትግርኛ አጣቃቀም ዘይቤ እና ቃላቶች ፤ጭራሽኑ የእንደርታ/ራያ/ተምቤን... ሰዎች አይመስሉም። የ15ዓመት፤ የ13፣ 10፣ 5 አመት... በረሃ መቆየት እንዴት ወደ እራስነት ማጣት ባሕሪ እና የራስ ጥርጣሬ ባሕሪይ ሊከሰት ቻለ? የሚል ጥያቄ ይጭርብኛል። የእነ መለስ አና የእነ የአባይ ፀሐየ፤ ስብሓት ዓሸዓዊ ልሳን ‘በእንደርታዊያኖቹ፤ በእነ ገብሩ አስራት፤ መስፍን (ጀኔራል) (ዐዲ ጉዶም)፤ ሙሉጌታ አብርሃ /ማንጁስ፤ (እንደርታ) ዐዲጉዶማዊው/እንደርታዊው መድሕን.. ወዘተ “ምላስ” ላይ **ምን የሚባል አስገዳጅ መርፌ ምላሳቸው ላይ ስለተወጉ ነው፤** የ “አ ሻ ዓ” ዎቹ የእነ አባይ እና የነመለስ ዜናዊን ልሳን እና የኤርትራዊያኖቹ የነ ኢሳያስ አፈወርቂ የቃላት ልሳን ተሸክመው “ከተማ ገብተው እነሱን የወለደ እንደርታዊው እና የራያዊው ገበሬ እና የከተማ ሕዝብ በዛው ልሳን ሊያነጋግሩት የተገደዱት?

ገብሩ አስራትም ሆነ ስዬ፤እንዲሁም ራያዊው ወያኔው ጀኔራል ጻድቃን ገብረተንሳይ የሚጠቀሙበት የትግርኛ አጣቃቀም ዘይቤው አንደ ምሳሌ ብትወስዱ ፤ ተምቤናዊው፤አንደርታዊውን እና ራያዊውን ልሳኖቻቸውን እና የቃላት አጣጣላቸውን አሸቀንጥረው ለመጣል ለምን እንደመረጡ እኔ ራሴ አጅግ በጣም ይገርመኛል።

አብዛኛዎቹ ከእንደርታ/ራያ/ተምቤን ..በመጉረፍ ወደ ወያኔ የተቀላቀሉ በሺ መቶዎቹ የሚቆጠሩ ታጋዮችም የራሳቸውን ያካባቢ “ድምፀ ቃላትና የአጠቃቀም” ዘይቤ በመተው ወደ አ .ሸ .ዓ ወይንም ወደ ኤርትራዊያኖቹ አዘምብለው ከጫካው ወደ ከተማ በመግባት “ሕጂ ሚጂ፤ መዚ፤ጊስ፤አልግስ፤ ዓሚል” ሲሉ ይደመጣሉ።ለምን? ምን ተገኘ?

አንድ ቀን የገጠመኝን ላወራችሁ፤፡ መቀሌ የሚገኘው አንደርታዊው የትግርኛ ‘ኤፍ ኤም’/የወያኔ ሬዲዮ አዘጋጅና ጋዜጠኛ የሆነው (ለጊዜው ስሙን ረሳሁት) የወያኔ አወዳሽ የሆነችውን “ኤደን ገብረስላሴ” የተባለቺውን ወጣሁ ወጣሁ የምትል ወጣት አንደርታዊት ቃለ መጠይቅ ሲያደርግላት፤ሁለቱም አንደርታዊያኖቹ በቃለመጠይቁ ሂደት “የራሳቸውን ልሳን ትተው “አሸዓ” እና “ኤርትርኛ” ለመሆን ሲታገሉ አድምጬአቸው፤ “ምን ለመሆን እየቃጣችሁ ነው? እራሳችሁ ለመሆን ለምን አትሞክሩም?” ብየ በኢመይል ጠይቄው ነበር። ትግርኛ ትግርኛ ነው ብሎ ሲመልስልኝ፤ “ትግርኛ አንድ አይደለም፤ እስከስታው ልሳኑ፤ አጣቃቀሙ፤ የከበሮ አመታተሙ/አጐሻሸሙ ዘይቤው ካውራጃ አውራጃ ይለያያል” ብየ ስመልስለት። “የሚመልሰው መልስ በማጣቱ “በዛው ጭጭ ብሎ ቀረ”።

ትግረኛ ትግርኛ ነው ይሉናል። አንድ ነው ይሉናል። እርግጥ ሰው፤ ሰው ነው። መኪና መኪና ነው። ነገር ግን ሰው ሁሉ የሚለየው ብዙ ነገሮች አሉዋቸው እና አንድ አይደሉም። ለምሳሌ ሁለት በ 'ሓጎስ' ስም የሚጠሩ ትግሬዎች ስማቸው አንድ ነው፤ ሁለቱ ሓጎሶች ግን የሚለያቸው ብዙ ነገሮች/ ባሕሪዎች አሉዋቸው። ትግርኛ አንድ አይደለም። የትግርኛ እስክስታም ሆነ የከበሮ አመታት ሳይቀር ይለያያል። አብዛኛው የተምቤን ሕዝብ ትግርኛ ተናጋሪ ነው። እስክስታው ግን ከሚታወቀው የትግርኛ "ኲዳ/ትልሂት" ጭረሽኑ የተለያ እና የማይመሳሰል ነው። አንዱ ትግሬ ከየትኛው አውራጃ እንደሆነ ከሚያወጣቸው ቃላቶችና ልሳኖች መለየት ትችላለህ። መለያው ነውና ሆን ተብሎ "በድርጅታዊ ሴራ" ያንን ማጥቃት ተገቢ አይደለም።

ስለዚህም ነው ትግርኛ ትግርኛ ነው፤ እስክስታ አስክስታ ነው፤ የከበሮ አመታት ቃናው አንድ ነው፤ የሚል የወያኔዎች ሙግት የማልቀበለው። የከበሮ አመታትም ሆነ እስክስታ አወራረድህ ትክክል አይደለምና የኔ አውራጃ ነው ትክክል እና የኔን ውረስ ማለት ሕጋዊ ነው? አንድ ስላልሆነ ሕጋዊ አይደለም። ራያ ትግርኛ ተናጋሪ ነው፤ ነገር ግን ከሌሎቹ ይለያል። ስለ ተለየ ወይንም አማርኛ ስላለበት/ኦሮምኛ ስለሚገባበት ወይንም የራሱ ዘይቤ ስለሚጠቀም፤ አነጋገርህን ለውጥ ማለት ሕጋዊ አይደለም። ወይንም በእስክስታው አወራረዱም ሆነ በአለባበሱ ስለሚለይ ትግርኛ ትግርኛ ነው እና የራያውነ የእንደርታው ወደ "ኢ. ሽ. ዓ." ወይንም ወደ ኤርትራኖቹ ( ወደ "አሎራዎቹ") አለባበስ፤ልሳን እና እስክስታ አወራረድ ቢለውጡ አንድ ችግር የለበትም ማለት አንችልም። በተፈጥሮ የግብይት የ አኗኗር ግንኙነት ከሆነ ምንም ችግር የለውም፤ ነገር ግን በሴራ እና በሕግ አስገድዶ መለወጥ ግን ወንጀል ነው።

አሁንም ልድገመው!!! ያንድ አካባቢ ልሳንና ለዘመናት የቆየ ጸንቶ ተቀባይነት አግኝቶ መረዳጃ ሆኖ የቆየ ያካባቢ ልሳን፤ አለባበስና የቃላት አጠቃቀማቸውን በሕግ መለወጥ ወንጀል ነው። የራያ ሴት/የእንደርታ እናቶች ቁንድላ አሰራር እና የ "አሽዓ" እናቶች ቁንድላ /ሽርቦ አሰራር እጅግ ይለያያል። ስለዚህ ያንቺ ትግርኛ ሽሩቦ አይደለም ይሄ ነው ትግርኛ ሹሩባ ማለት ይቻላል? ቋንቋን የማጽዳት ዘመቻ እያደረጉት ያሉትም ይኼው ነው። ወያኔዎች እጃቸውን ከዚህ ወንጀል ስራ እራሳቸውን ማግለል ይጠበቅባቸዋል። ሕዘብ የወያኔ ንብረት ወይንም የግል ህንፃ አይደለም። ማንም መንግሥት/ድርጅት ሊጋፋው የማይገባ የራሱ ባሕላዊ መዝጊያ/አጥር አለው።

ለመግቢያ ይህ ካልኩ ዘንዳ የቋንቋ ጽዳት ዘመቻ ከሚያካሂዱት ወያኔዎች መካካል አዛውንቱ ገብረኪዳን ደስታ ሰሞኑን ደግሞ በትግርኛ ቋንቋ **"እምቢታ አንጻር ወረርቲ"** የሚል ስለ **አጼ ዮሓንስ** አዲስ መጽሐፍ በመጻፉ "ዛሬም **አፄ**

**ምኒልክን**" በጥላቻ መንፈስ ከአፉ አኘኮ ያልጠገባቸውን የኢትዮጵያ ንጉሥ ከዮሐንስ ጋር ያነጻጸረበትን ሞኛ ሞኝ ብሔረተኛነቱን ዛሬም ምን እያለ እንደሆነ እስቲ እንድናዳምጥለት። "አይጋ ፎረም" ከተባለው የወያኔዎች ድረገጽ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ እስኪ አንድ ባንድ የተናገረውን ተርጉሜ ላቅርብላችሁ እና የራሳችሁን ግንዛቤ ውሰዱ።

አይጋፎረም- ጥየቄ:- 'አምቢ ለወራሪዎች' የሚል መጽሐፍ ጽፈዋል ፤ ስለዚህ መጽሐፍ ጉዳይ ሚሉን ነገር ካለ ቢነግሩን?

ገብረኪዳን፤-ይህ መጽሐፍ ለመጻፍ የወሰንኩበት እና ያስገደደኝ ምክንያት፤ የአጼ ዮሐንስ ተገቢውን የታሪክ የክብር ቦታ አጥቶ ለ124 አመት ወደ መድረክ ሚያስተዋውቀው አጥቶ ተቀብሮ ስለሚገኝ፤ 'እንቅልፍ ስላሳጣኝ' የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪ ኢትዮጵያዊያኖች፤ "ታሪካቸውን (የአጼ ዮሐንስን ታሪክ) ማውሳት ይቅርና "ንጉሥ ነገሥት እንደነበሩ እንኳ አያውቋቸውም"። የሌለቹ ነገሥታት ገድል ሲወሳ ሁሌም ሆን ብለው አጼ ዮሐንስን ይዘልዋቸዋል። በዱሮው የኢትዮጵያ ቴ/ቪ ሳይቀር "ቴድሮስ ብለው ወደ ሚኒልክ፤ ከዚያ ወደ ሃይለስላሴ በመዝለል ዮሐንስን ዘልለው ወደ ሌሎቹ ይሻገራሉ"።ምንም ቢሆን! ዮሐንስን አያነሷቸውም። ይህ ድርጊት ያሳዝነኝ ስለነበረ፤እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ በዚህ ምክንያት ነው ይህንን መጽሐፍ ልጽፍ የቻልኩበት መነሻ።

(ከተርጓሚው:- በዚህ ላይ አንድ ማለት እፈልጋለሁ- አትላንታ አሜሪካ ውስጥ የወያኔ ጀሌዎች 38ኛው የወየኔ በዓል ሲያከብሩ ለዝግጅቱ የቀረበው ታሪክ የሚተነትን የቪዲዮ ዝግጅት ላይ ቴድሮስን፤ዮሐንሰን ካሳየ በኋላ....ምኒልከን ዝሎ ወደ መለስ ዜናዊ በመሻገር ከዚያ ...ወደ ወያኔውዎቹ ወደ ሓየሎም አርአያ.. ከዚያ ወደ ተራ ታጋዮቻቸው ወደ እነ "አሞራ"... እያሉ ወደ እሚጠሩት የወያኔ ታጋይ ነበር ሲያሳዩ የነበረው። ይህንን በሚመለከት አንድ ሃተታ አዘጋጅቼ ለመለጠፍ ስዘጋጅ ፤ የገብረኪዳን ደስታ ቃለ መጠይቅ ጊዜየን ስለተሻማብኝ በዚህ የምለው ስላላ በይደር ስለቆየሁት፤ ቆዩኝ። ወያኔዎች ገብረኪዳን ለሚለው "አጠፉ/ብድር መመለሻ/ በምኒልክ ላይ ጥላቻ እያስፋፉ "የትግሬ እናቶቻችን ማህጸን በጣሊያን ወረበላ ከመደፈርና ከጣሊያን ሶላቶ አንደ ኤርትራኖቹ ከመደቀል ነፃ ያወጡንን አምየ ምኒልክን" ማውገዝና በታሪክ ዝግጅት እና ማሕደር ላይ ሳያወሷቸው እየዘለሉ፤ ስማቸውን በማይገባ በመበከል፤ አዲሱ ትውልድ በጠላትንት አንዲያያቸው እየመረዙት ለመሆኑን የገብረኪዳን ደስታ አነጋገር ተግባራዊ አንዴት እንደሆነ ከአትላንታ ጀሌዎች ላይ መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ላይ "Would you not wish Menlik the lion who liberate Tigrayans from Italian colonization reject the request for help by Tigray rulers to remove Italians from Tigray in 1888- that Tigrayans are now arguing Italian in Adua was not Menlik's lead army, but Tigrayan's lead army defeated Italian? what could have happened if Menlik could have refused to come to Tigray? የሚል ጽሑፍ አዘጋጅቻለሁ። እስከዛው ድረስ ግን የ አትላናታ ጀሌዎች ጸረ ሚኒልክ ለማንጸባረቅ ያቀረቡት የታየው የስዕለ ድምጽ/ቪድዮ ዝግጅት

ለመታዘብ ይህንን ተመልከቱ። Lekatit 11 Celebration in Atlanta 2013 http://youtu.be/-wnp85RVELw በዚህ ቪዲዮ ላይ አምዬ ምኒልክን ታጥዋቸዋላችሁ። ምኒሊክ በሐዮልም፤ በአሞራ፤ የወያኔ ተጋዮች እና ለሻዕቢያ ህይታቸውና ላባቸው ያበረከቱ በአሳፋሪ ትውልዶች ተተክተው ስትምለከቱ በጣም አስቀያሜ ትውልድ!!!ማለት ሲያንስ ነው። አሁን ወደ ቃለ መጠይቁ እናምራ።

**Geberekidan Desta interview with Aigaforum 3 21 2013**

**ጥያቄ፡-** አፄ ዮሐንስ ማለት ማናቸው?

**ገብረኪዳን፡-** በታሪክ ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ ሕልውና ለግብይት ድርድር የማያቀርቡ፤ንጉሠ ነገሥት የነበሩ ናቸው። ይህ ብቻ አይደለም የሚገልጻቸው። ንጉሠ ነገሥት የሚል ቃል እነ ሚኒሊክ፤እና አጼ ሃይለስላሴ ሲጠቀሙበት የነበረ የንግሥነት ማዕርግ ነው። ንጉሠ ነገሥት የሚያስብላቸው ታሪክ ግን አልነበራቸውም። ምክንያቱም ነጉሦች አልሾሙም። ንጉሠ ነገሥት የሚል ስም እንዲኖረው የሚገባው መሪ፤ለምሳሌ ዮሐንስ ነጉሶችን ሾመው ነበር። ሚኒሊክ ንጉሡ ሸዋ፤ ተ/ሃይማኖት ንጉሠ ጎጃም፤ ወዘተ ..ሾመዋል። ዮሐንስ ኢትዮጵያን “በፌደራላዊ” ስርዓት ያነጸ ንጉሠ ነገሥት ነበር።

**ጥያቄ፡-** በዘር የንግሥና ዘር ነበራቸው?

**መልስ፡-** እነዚያ በዘር ንግሥና ነበረን የሚሉ ሃይሎች የንግሥና ዘር እንደነባራቸው አኔ በግሌ አላምንም። ነገር ግን እራስህ ብድግ ብለህ ባሕታዊያን አሰልፈህ፤ ሰብከህ ፤ የንገሥታት ዘር አለን ማለት ይቻላል። አፄ ዮሐንስ “አፍራከዊ” ናቸው። የሰለሞን ልጅ ነኝ፤ የሰሎሞን ዘር ነኝ፤ ምንትስ ምንትሴ አይሉም። ወደ ዱርቡሽ መሪው ወደ “አቡ አንጃ” የጻፉት ደብዳቤ ላይ ብትመለከቱ “ሁላችንም የካም ልጆች፤ አፍሪካዊያን ነን” ነው የሚሉት ። እንደ ሌሎቹ “ሞአ አንበሳ” አይሉም። ስለዚህም “አፍሪካዊ” ናቸው።” ባፍሪካዊነትም ፤በኢትዮጵያዊነትም እንጂ “ወደ እስራኤልነት ነኝ የማለቱ ምናምን የማይቃጣቸው ንጉሠ ነገሥት ነበሩ አጼ ዮሐንስ።” (ምስኪኑ ገብረኪዳን ደስታ የእስራኤልነት ዘር ማን እንዳመጣው ስረ መሰረቱ የት እንደተጀመረ እና መፈክሩ ለተቀሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት ማን እንዳስተዋወቀው አላወቀውም። ይህንን መፈክር በሚያስተጋቡ ነገሥታት ላይ በማናናቅ ለምኒሊክ ሲያከናንባቸው የራሱን አክሱማዊያን ትግሬ ነገሥታት እና ዮሐንስን ይህንን መፈክር ይጠቀሙ እንደነበር አላወቀውም። በመሰረቱ ‘ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ’ የሚለው መፈክር ትርጉሙ ገብረኪዳን ሆን ብሎ እያወቀ  አጣምሞ አቀርቦታል እንጂ ትርጉሙ ሌላ ነው። ሲያስፈልግ ሰፊውን ዝርዝር ማቅረብ ይቻላል። )

**ጥያቄ፡-** መምህር ገብረኪዳን ፤ አጼ ዮሐንስ ማን ነው የገደላቸው? እርግጠኛ መረጃስ አለ?

**መልስ፡-**መቸም የጽሑፍ መረጃ እንደሚያመለክተው "አፈወርቅ ገብረየሱስ የሚሉት "ደካማው ድርቡሽ አይደለም የገደላቸው፤በአፄ ምኒልክ ብርታት ነው የተገደሉት ነው የሚለው። ተክሌ የሻው የሚባል ጸሐፊም፤"ሃይማኖትዎን ይቀይሩ ምናምን ምንትስ ተብለው ከድርቡሽ ጋር በመሰለፋቸው" *(ገብረኪዳን እዚህ ላይ አቶ ተክሌ የሻው በቅጡ የጻፉትን እንኳ መጥቀስ ስላቃተው - ምን ለማለት እንደፈለገ በትግርኛውንም ቢሆን የተስተካከለ አረፍተ ነገር ማስተካከል ስላቃተው ለትርጉምም አይመችም እና እንዳው በግርድፉ እሱ እንዳለው ተርጉሜዋለሁ)* ነው የገደሏቸው ሲል ጽፏል።

... ይህንን በሚመለከት እኔ የማውቀው ነገር የለኝም። የትግራይ ሕዝብ የሚለው ግን አለ። የትግራይ ሕዝብ የሚያምነውና የሚለውን በመጽሐፌ ጠቅሼዋለሁ። ይኼውም፤ መተማ ላይ አጼ ዮሐንስ እና ሠራዊታቸው ድል ተጐናጽፈው ነበር። አጼ ዮሐንስን የመታቻቸው ጥይት ፊት ለፊት በተተኮሰች ጥይት ሳይሆን ከኋላ በተተኰሰች ጥይት ተመትተው ነው የሞቱት። ስለዚህም ከወደ ኋላቸው የተተኰሰቺው ጥይት ከአጼ ዮሓንስ ጠላቶች የተተኮሰች ጥየት ነች ነው የሚባለው፤ የትግራይ ሕዝብም ይህንኑ ነው የሚለው። የአጼ ዮሐንስ ጠላቶች ደግሞ እነማን መሆናቸው የታወቀ ነው።

**ጥያቄ፡-** ያገር ውስጥ ጠላት ማለት ነው?

**መልስ፤**- አዎ!

**ጥያቄ፡-**አፄ ዮሐንስ በዘመነ ንግሥነታቸው ጊዜ ከአፄ ቴዎድሮስ እና ከነ አፄ ምኒልክ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ምን ይመስል ነበር?

**መልስ፡-** በዘመነ አፄ ቴዎድሮስ ጊዜ ደጃዝማች በዝብዝ ካሳ ለቴዎድሮስ አልገዛም ብሎ አሻፈረኝ በማለት ሸፈተ።ሌሎች የኢትዮጵያ መሳፍንትም እንደለ በሙሉ ሸፍተ። የጎንደር ሕዝብም ሸፍቷል።የጎንደር ሕዘብም አፄ ቴዎድሮስን ወደ ደብረ ታቦር አባረራቸው።ምክንያቱም ጎንደር ውስጥ የነበሩት አብያተ ክርስትያናት ስላቃጠሉባቸው፤ 2 አብያተ ቤተክርስትያናት ብቻ ሲቀሩ የተቀሩት አወደማቸው፤አቃጠላቸው።ይህ ድርጊት ፈጻሚው ቴዎድሮስ ነው።

ወደ ደብረ ታቦር ከሄደም በኋላም ቢሆን ከዛሬ ቀን ጀምሮ በቅሎ ፈረስ "እህል" እንኳ "ሳር" እንዳይመገቡ ብሎ ስላወጀ፤ሕዝብ በዚህ የተነሳ ስለተበሳጨ ፤ አሁንም ከደብረተባር አስወጥቶ እንዲባረር አደረገ።ከዚያ በኋላ ወደ መቅደላ ተራራ ሄዶ መሸገ።መቅደላ ላይ 7000 ሠራዊት ይዞ እዛቺው ይኖር ነበር።

በዚህ ብቻ አልተወሰነም፡የውጭ ዜጎችም አስሮ በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ አደርጎ ነበር።እንኚህን እንዳሰረ፤ ዋግ ሹም ጐበዜን (በኋላ ተክለ ገዮርጊስ የተባለው) እና ምኒልክ ንጉሥ ሸዋ ግምባር ፈጥረው 'በወቅቱ የመን አገር /ዓደን/ ውስጥ ሲኖር ወደ ነበረው የእንግሊዝ ወኪል ግንኙነት በመፍጠር፤ በቴዎድሮስ ቁጥጥር ያሉት መቅደላ ላይ የታሰሩ ዜጎቻችሁ፤ እኛ አንናንተ ጋር ሆነን እናስፈታላችኋለን እና ኑ በማለት እንግሊዞችን ወደ አገር እንዲመጡ ሁለቱ የውስጥ ሴራ በመጐንጐን እንግሊዞች እንዲመጡ አደረጉ።

ይህ እኔ የምለው ሳይሆን 'በሰነድ ላይ የሰፈረ ጽሁፍ ነው"። በኋላ እንግሊዝን በመጋበዝ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ጀኔራል ናፔር "ዙላ" ወደብ ላይ እንደደረሰ፤ "ቁም አንጂ እንዴ! ወዴት እየሄድክ ነው?" ተብሎ ዙላ ላይ ሲጠየቅ "ዜጎቻችን ቴዎድሮስ አስሮብናል እና ሄደን ለማስፈታት ሁለቱም ማለትም ዋግ ሹም ጐበዜ እና ምኒልክ የሚያስተዳድሩት ግዛት ስለሆነ አንድንገባ ፈቅደውልናል።" አሉዋቸው። "የለም ትግራይ ትግገርኚ እኮ የእነሱ ግዛት አይደለም" በዚህ ማለፍ አትችሉም የሚል መረጃ ተነገራቸው። ታዲያ እንዴት እናድርግ ብለው ሲጠይቁ: "ግዛቱ የአባ በዝብዝ ስለሆነ ትግራይን ለማቋረጥ አባ በዝብዝብ ማስፈቀድ አለብህ፤ ካልሆነ አታልፍም ተባለ"። ይህ ሲሆን "አባ በዝብን አገኙት"። ከዚያ በኋላ" እንምታው/አንውጋው ወይስ.....? እንዲሁ እንዲያልፍ አንፍቀድለት?" ተብሎ ውይይት ተደረገ። አይ "መምታት አንኳ በተገባን ነበር ፤ነገር ግን ምን አገባን፤ በኋላ ደግሞ ቴዎድሮስ መጥቶ ቤተክረስትያናችንን ሊያቃጥልብ ነው እና እንግሊዝ " የራሱን ዜጐች አንዳስፈታ ወዲያውኑ ወደ አገሩ በመጣበት እንዲመለስ እኛኑን አንዳይወጋን የፈርምልን ተብሎ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ፤ እንግሊዝም " እኔ ዜጎቼን ከማስፈታት ሌላ ዓለማና ፍላጐት የለኝም" በማለት "ሙሉ ሐላፊነት" በመውሰድ የትግራይ መሬት አቋርጦ እንዲያልፍ ተፈቀደለት።

*(ገብረኪዳን የሸሸገን ሁለት ነገሮች አሉ፡ 1ኛ ሙሉ ሓላፊነት ወስዶ የሚለው የስምምነት ምን እንደሚዘረዝር እና ፌርማ ቀን እና የት እንደተደራደሩ አልነገረንም። ሌላው 2ኛው ነጥብ እኔም ሆነ እናንተ የምናውቀው እዛው በግብዣው ላይረ የነበሩ በእንገሊዞቹ እና በሌሎች ባእዳን የተጻፈ ታሪክ እና በፈረንጆች በ 1868 የተጻፈ እንግሊዝ አገር የታተመ የእንግሊዝ አገር መጽሔት (አንድ ወዳጀ ልኮልኝ በእጀ ይገኛል) የሚነግረን ነገር "ዮሃንስ የቅድመ አያታቸው መኖሪያና ትውልድ ስፍራ (ደጃች ወልደስላሴ) በነበረቺዋ "ሕንጣሎ" የምትባለዋ ከዳገት ሥር የምትገኝ ትንሽ ገጠር፤ ላይ የተንጣለለ ደንኳን ዘርግተው ጠጅ እና ሰንጋ ተጥሎ፤ የቀለጠ ድግስ አድርገው ሰንቁን አዘጋጅተውለት በሰላም አንደሸኙት እየታወቀ፤ ገብረኪዳን ስለ እዚህ ጉዳይ ሳይነገርን፤ ወደ ዋግ ሹም በመዝለል፤ ዋግ ሹም ጐበዜን በስንቅ አቅራቢና በስተናጋጅነት ሲካሳቸው ያሳዝናልም ያስቃልም፤፡ ይህን በተመለከተ ከዚህ በታች ያለውን የገብረኪዳን አደሎአዊ ብሔረተኛነትን አድምጡ።)*

የዋግ ሹም ጐበዜ ግዛት እንደደረሰ፤ዋግ ሹም ጐበዜ፤ ሰንቅና ምግብ እየሰጠ የዋግ ሹም ሰራዊት እና ተባባሪዎቹ እንዲሸኝዋቸው በማድረግ እስከ መቅደላ አደረሳቸው። ምኒልከም ሠራዊቱ ይዞ መጣ። ዋግ ሹም ጐበዜም እንዲሁ ከጐንህ ጋር ሆነን ቴዎድሮስን ወግተን ዜጎችህን ነፃ በማውጣቱ ረገድ እንርዳህ ብለው ሁለቱም እንግሊዘን ሲጠይቁት፤ “አይሆንም፤ራሴ እችላለሁ” በማለት እምቢ አላቸው።

እንግሊዝ ቴዎድሮስን ድል መትቶ ዜጐቹ ነጻ ካወጣ በኋላ፡ ምኒልክ ወዲያዉኑ “ለእንግሊዞቹ ደብዳቤ በማስያዝ የእንኳን ደስ አላችሁ መልእክት ወደ ንግሥት ቪክቶሪያ ላከላት።” ስለዚህ “አባ በዝብዝ ካሳ” እንግሊዝን በመጋበዝ ጥሪ በማድረግ እንዲመጡ አላደረገም። መንገድ መርቶ እስከ መቅደላ ድረስ አልሸኘም፡፤ ያደረጋት ነገር ብትኖር ፤በአገሬ ግዛት ማለፍ ትችላላችሁ ብሎ ፈቅዶላቸዋል። ስለሆነም እነኚህ አባ በዝብዝ ካሳን (አፄ ዮሐንስ) እንግሊዝ አስገብተዋል፤ እያሉ የሚከሱ “የትግራይን ሕዝብ ዘላለም ደም እየከፈለ፤ መከራውን እንድያይ የሚፈልጉ ያልሆነ ታሪክ እንዲመዘገብ የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው እንዲህ ያለውን ውንጀላ የሚከሱ።በዝብዝ ካሳ እንዲያለው ነገር የለውም!!!

በማለት ጐጠኛው መምህር ገብረኪዳን የብሔረተኛ መለያ የሆነው “የትግሬ ነገሥታት ከደሙ ንጹሓን ናቸው’ የነኛ የአማራዎቹ እና የአጐቦቹ ነገሥታት ግን ብሔራዊ ወንጀል የፈጸሙ ናቸው። በማለት የሰለቸንን ጭብጥ የሌለው የተዛባ መረጃ እና ውሸት ዛሬም በመደጋገም ለማያውቁ አድማጮቹ ለመመረዝ በመነሳሳት “ኤጼ ዮሐንስን ስም በወርቅ ቀባብቶ” እንግሊዝን አልጠሩም፤ ለእንግሊዝ ምግብ አላቀረቡም፤ መንገድ አልሸኙም,,,ወዘተ..ወዘተ… የሚለው “ዮሐንስ ባዕደን በማስገባትና በመጋበዝ፤ድርድር በመፈጸም፤ጠላትን መንገድ ጠርጎ፤ ሸኝቶ፤አሳይቶና፤ደህነነቱን አመላክቶ ትብብር ያሳየ “የካባቢ/ያገርመሪ” የሚያስከስስ ወንጀል” መሆኑን እየታወቀ የዮሐንስ ትብብር አሳንሶ በማጣጣል በጣም አስቀያሚ የሆነ ዘመኑ ያለፈው የፌውዳል ብሄረተኛ መስመር ይዞ ያንን የበሰበሰ የደም እና የአጥንት ቆጠራ ወገንተኛነት አጥር በማበጀት የታሪክ አተላውን ሲደፋብን መስማት “እኔስ አቅሻለሁ ለማያውቅሽ ታጠኚ” የሚያሰኝ ነው። ግብዣ በተጋበዙት ተጋባዦቹ የተጻፈ በ1868 የታተመ መጽሔት ሰነድ አለ።

አይጋ ፎረም ላይ የተለጠፈው አሳፋሪ የትግርኛ የተዛባ የታሪክ ቃለ መጠይቅ ገብረኪዳን ምን እንደሚል አብዛኛዎቻችሁ ትግርኛ ለማታዳምጡ ዜጎች ባለ ማዳመጣችሁ ለማወቅ ፈልጋችሁ የቆጫችሁ ዜጎች ካላችሁ ፤ ይኼው የትግርኛው ቃለ መጠይቅ ትርጉም ወደ አማርኛ ተርጉሜ እንድታነብቡት አድርጌአለሁ። በገብረኪዳን ደስታ ቃለ መጥይቅ ለመተቸት የምትሹ ሰዎች ካለችሁም ይኼው በሩን ከፍቼላችኋላሁ።

**የግል ማስታወሻ፤ ለወዳጆቼ፡**

በዚህ ወር በጣም ሲበዛ የተወጠረ ጊዜ ስላለኝ ፤መፈናፈኛ አግኝቼ በሰፊው ስለ ቃለ መጠይቁ እስክመለስበት ጊዜ ሌሎቻችሁ በዚህ የምትሉት ነገር ካለ ፤በሩ ይኼው። ስልክ በመደወል  መጽሐፍ ለማግኘትም ሆነ በተለመደው ክፍለ ጊዜ ድምጽሕ እየራቀን ሄደ ምነው ተወዳጁ ጽሑፍህን እና ክርክርህን ያለ ወትረው እራቀን በማለት የደዋለችሁልኝ እና የስልክ ጥሪአችሁን በውቅቱ መልእክታችሁ ወዲያውኑ አግኝቼ በወቅቱ ባለመመለሴ ይቅርታ እጠይቃለሁ። አሁንም ከከተማ ወጣ ወጣ እያልኩ ፋታ ስላላገኘሁ፤ በትእግስት እንደምትጠብቁኝ ተስፋ አደርጋለሁ። “ጠባብ ብሔረተኛነት የታሪክ አታላ ነው!!” “ኢትዮጵያዊነት አሸናፊ ነው!!!”

ጌታቸው ረዳ www.ethiopiansemay.blogspot.com getachre@aol.com